**የDC የህዝብ ቤተ መጽሀፍት**
**የአርት(ሥነ ጥበቦች) እና ኤግዝቢሽኖች ፖሊሲ**

1. **መግቢያ**

   የ DC የህዝብ ቤተ መጽሀፍት (DCPL) አርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶችን እንደ መማርያ፣ግኝት፣እድገት፣እና መገናኛ ምንጭ ያከብራል። ይህ ፖሊሲ የሥነ ጥበብ እና / ወይም የኤግዚቢሽን ስራዎችን የምንመርጥበት፣የምናቀርብበት እና/ወይም የምናበድርበት ዘዴዎችን ያሳያል። ፖሊሲው በDCPL ላይ ያሉ የሥነ ጥበብ እና የኤግዚቢት ስራዎች ከDCPL ባህላዊ ፕሮግራሞች ጋር የተዋሃዱ እና ስትራቴጂካዊ ጥቅማቸውን የሚያራምዱ መሆኑን ያረጋግጣል።

   በማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር የመታሰቢያ ቤተ መጽሀፍት ጋር ካለው ጠንካራ ፕሮግራም በተጨማሪ፣በታው በሚችለው አቅም አርት(ሥነ ጥበብ) የእያንዳንዱ የአካባቢ ቤተ መጽሀፍት ገጽታ መሆን አለበት። ይህ ቋሚ የአርት(ሥነ ጥበብ) ሥራዎችን፣የረጅም ጊዜ የአርት(ሥርነ ጥበብ) ውሰቶችን፣ እና ጊዜያዊ ትርዒቶችን ያካትታል።

   በማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር ቤተ መጽሀፍት ውስጥ ያሉ ኤግዚቢቶች የዲስትሪክቱ ኗሪ የዲስትሪክቱን ያለፈ ታሪክ ያለውን እውቀት ለማስፋት ቁልፍ ነው እና በዲስትሪክቱ ያሁን እና የወደፊት እጣ ላይ የመሳተፊያ ፖርታል ነው። በተጨማሪ ቦታው ሲፈቅድ ኤግዚቢቶች በአካባቢው ቤተ መጽሀፍት ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ።

2. **ይዘት እና የመግለጽ መብት**

   የአርት(ሥነ ጥበብ) እና የኤግዚቢት ፕሮግራሙ እንደ የምስል፣ትርዒት፣መልቲሚዲያ፣እና ማህበረሰብ አቀፍ የተለያየ ቅርጽ ያላቸው በርካታ ዓይነት ቋሚ እና ጊዜያዊ ስራዎችን ያካትታል። በDCPL ውስጥ ያሉ አርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶች ሰፋ ያለ ማእቀፍ ያላቸውን እይታዎች፣መግለጫዎች፣አስተያየቶች እና ፍላጎቶችን የሚያንጸባርቁ መሆን አለባቸው፣ እና ይዘታቸውም አነቃቂ ሊሆኑ ይችላሉ። DCPL በይዘትም ሆነ በቅርጽ ላይ ያለ ገደብ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትን ያበረታታል። የDC የህዝብ ቤተ መጽሀፍት በአሜሪካ ቤተ መጽሀፍት ማህበር (ALA) በ“Visual and Performing Arts in Libraries: An Interpretation of the Library Bill of Rights” ያሉ መርህዎችን ያከበራል።

   በቤተ መጽሀፍቱ የሚታዩ ስራዎች ላይ የተገለጹ አመለካከቶች የፈጠራ ባለቤቱ ናቸው እና የD.C. መንግስት፣ቤተ መጽሀፍቱ፣ የባለአደራ ቦርዱ፣አስተዳደሩ ወይም ሰራተኞች ላይሆኑ ይችላሉ። የDC የህዝብ ቤተ መጽሀፍት አርት(ሥነ ጥበብ) እና የኤግዝቢሽን ፕሮግራም ሁሉንም የD C  መንግስት ፖሊሲዎች፣ደምቦች እና ህጎችን ያከብራል።

3. **ብዝሀነት፣እኩልነት እና አካታችነት**

   ቤተ መጽሀፍት አርት(ሥነ ጥበብ) ሁሉንም የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ዜጋዎችን ያካተተ ለማድረግ ይተጋል። እያንዳንዱ የDC የዲስትሪክት ኗሪ በDC የህዝብ ቤተ መጽሀፍት ባህላዊ እንቅስቃሴዎች የመደሰት ፣ የመሳተፍ እና የመጠቀም መብት አለው።

ቤተ መጽሀፍቱ የዲስትሪክቱ ኗሪዎችን በርካታ ታሪካዊ አመጣጥን እና እድገቱን የቀረጹ በርካታ ባህሎችን በመለየት፣
የታሪክ ብዝሀነትን ያከብራል። DCPL
የአካባቢ ባህላዊ ማንነት እና ባህሎችን አስፈላጊነት እና
ለባህል እውቅና መስጠት የሲቪክ ተሳትፎ እና ማህበረሰብን
ለማበልጸግ ያለውን ሚና ያረጋግጣል። በአርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶቻችን አማካይነት፣በከተማችን ውስጥ ያለውን የባህል እና የማንነት ብዝሀነትን እውቅና ለመስጠት እና ከፍ ለማድረግ፣የዲስትሪክቱን የበለጠ የፍትሀዊነት ግንዛቤ ለመደገፍ እናልማለን።

እኛ ዝቅተኛ አገልግሎት ሲሰጣቸው የነበሩ ማህበረሰቦችን ወይም ህዝቦችን የሚያገለግሉ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የአርቲስቲክ እና ባህላዊ እንቅስቃሴዎችን፣በተለይም የዘር ወይም የባህል ብዝሀነት ያላቸውን ለመደገፍ እናልማለን። በተጨማሪ ፓነል ሲመረጥ፣አርት(ሥነ ጥበብ) የሚቀመጥበት አካባቢ ወይም ማህበረሰብ ኗሪዎች፣እና የተለያዩ የባለድርሻ አካላት ተወካዮች መካተታቸውን ለማረጋገጥ እንተጋለን።

## 4. የአርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዝቢሽኖችን ለመግጠም ምደባ እና መመዘኛ

a. አርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶች ሊኖርባቸው የሚችሉ ቦታዎች የህንጻ ዲዛይን፣የተቋማት መመዘኛዎችን፣የተገልጋይ ልምድ፣ ክፍት ቦታ መኖር፣እና የደህንነት ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። የአካባቢ ቤተ መጽሀፍት በህንጻ አሰራር ዘይቤ፣መጠን፣እድሜ፣እና በሚያገለግሏቸው ማህበረሰቦች በጣም የሚለያዩ በመሆኑ፣በእያንዳንዱ ስፍራ ያለው የአርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዝቢት በጣም ይለያያል፣እና በአንዳንድ ህንጻዎች በጣም ውስን ሊሆን ይችላል።

b. ሁሉም አርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዝቢቶች የአርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶች ፖሊሲን ማክበር እና የቤተ መጽሀፍት ፕሮግራም ገጽታን መደገፍ አለባቸው። የሚገጠመው የአርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶች በተቻለ መጠን እያንዳንዱ እቃ ከሚቀመጥበት የቤተ መጽሀፍት ልዩ ስፍራ ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነት ሊኖረው ፣እና የአርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዝቢቶች ፕሮግራም ግቦችን ማሟላት አለበት።

c. አርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶች ሁሉንም ህጎች እና ደንቦች፣በተለይም ከነውረኝነት፣የቅጂ መብት፣ምልክት፣ስም ማጥፋት ወይም ሚስጥራዊነት መጻረር የሚመለከቱትን ማክበር አለባቸው።

d. ለቤተ መጽሀፍቱ የሚሆኑ አርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶች የሚመረጥበት መመዘኛ የሚወሰነው ከእያንዳንዱ ፕሮጀክት የግምገማ ኮሚቴ ጋር በመመካከር ነው። ለሁሉም ፕሮጀክቶች አጠቃላይ መመዘኛዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣አጠቃላይ ወጥነት፣ግልጽነት፣እና የእይታ ተጽእኖ፣ፈጠራ፣ስሜታዊ ተጽእኖ፣ለሰፊ ተመልካች ተደራሽነት ፤ባህላዊ ታማኝነት፤የአካባቢውን ባህል የማወቅ ልምድ፤እና እንደ አግባብነቱ የማህበረሰብ ተሳትፎ ። መመዘኛዎቹ በተመረጠ መስክ አርቲስቱ ወይም ዲዛይነሩ ያለውን የሞያ ስኬት ወይም የታወቀ እምቅ ችሎታን ማሳየት አለባቸው። ለእያንዳንዱ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ አውድን ተኮር ያደረገ መመዘኛ ሊኖረው ይችላል። አንድ ዕቃ ለመመረጥ ሁሉንም መመዘኛዎች ማሟላት

አያስፈልገውም። ሁሉም ምርጫዎች የHatch Act ን ጨምሮ የፌደራል እና የዲስትሪክት ህጎች፣ደምቦች እና ፖሊሲዎችን ማክበር አለባቸው።

e. እያንዳንዱ የአርት(ሥነ ጥበብ) ወይም ኤግዚቢቶች ወደ ቤተ መጽሀፍቱ ስብስብ በግዢ በቋሚነት ፣ወይም በጊዜያዊ ውስት በኮሚሽን፣ስጦታ፣ወይም ግዢ እንዲካተት የግምገማ ኮሚቴ ይቋቋማል። የግምገማ ኮሚቴው የሚዋቀረው የስትራቴጂክ አጋርነት ዳይሬክተር፣የዲዛይን አቀናባሪ፣እና ቢያንስ አንድ የቤተ መጽሀፍ ሰራተኛ፣ፍቃደኛ የማህበረሰብ አባል ወይም ለፕሮጀክቱ ቁልፍ የሆነ ባለድርሻ አካልን በማካተት ነው። እያንዳንዱ የግምገማ ኮሚቴ በፓነል ከማገልገላቸው በፊት የፍላጎት መጋጨት ቅጽን እንዲሞሉ ይጠየቃሉ።

## 5. **የአርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶች የመግጠም ሂደት**

a. DCPL የሚገጠሙ የአርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶችን የሚመርጥበት ሶስት መንገዶች አሉ፣
   i. DCPL ለሚገጠሙ የአርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዚቢቶች የጋራ ስፖንሰር በመሆን ሊያገለግል ይችላል።
   ii. DCPL የራሱን የአርት(ሥነ ጥበብ) መግጠም እና ኤግዚቢቶችን ሊያዘጋጅ ይችላል።
   iii. DCPL በDCPL ድህረገጽ ላይ ባለው የDCPL "የኤግዝቢት መመሪያዎች እና ሂደት" ላይ በተዘረዘረው የግምገማ ሂደት መሰረት ያልተጠየቀ ኤግዚቢሽኖችን ለማድረግ ሊወስን ይችላል። በቂ ምክንያቶች ከሌሉ በስተቀር ለአካባቢው ቤተ መጽሀፍት ያልተጠየቁ ጊዜያዊ ኤግዚቢሽኖች አይታሰቡም። DCPL በአጎራባች ቤተ መጽሀፍት ጊዜያዊ ፕሮግራም እንዲዘጋጅ የሚጋብዙ ቋሚ መሰርያዎችን አይገጥምም። ይህን ፖሊሲ ተጨማሪ ግብዓቶችን መሰረት በማድረግ በድጋሚ እናየዋለን።

b. ከ12 ወራት ***በላይ*** ለሆነ ጊዜ የሚገጠሙ መሳርያዎች ኤግዝቢሽኑ ከሚጀምርበት ቀን 60 ቀናት በፊት በዚህ ፖሊሲ ላይ በተቀመጡት መመዘኛዎች መሰረት ከህዝብ አገልግሎቶች እና ተቋማት አስተዳደር ጋር በመመካከር በዋና ዳይሬክተር፣በስትራቴጂክ አጋሮች ዳይሬክተር እና በዲዛይን አቀናባሪው መጽደቅ አለባቸው።

c. ከ12 ወራት ***ላነሰ*** ጊዜ የሚገጠሙ መሳርያዎች ኤግዝቢሽኑ ከሚጀምርበት ቀን 60 ቀናት በፊት በዚህ ፖሊሲ ላይ በተቀመጡት መመዘኛዎች መሰረት ከህዝብ አገልግሎቶች እና ተቋማት አስተዳደር ጋር በመመካከር በስትራቴጂክ አጋሮች ዳይሬክተር እና በዲዛይን አቀናባሪው መጽደቅ አለባቸው።

d. የተገጠሙ መሳሪያዎች ወቅታዊ፣አስፈላጊ እና በጥሩ ሁኔታ መቆየታቸውን ለማረጋገጥ ከህዝብ አገልግሎቶች እና ተቋማት አስተዳደር ጋር በመመካከር በስትራቴጂክ አጋሮች ዳይሬክተር እና በዲዛይን አቀናባሪው ፍቃድ መሳሪያዎቹ ሊሻሻሉ ይችላሉ።

e. የአርቲስት ወይም የኤግዝቢት ኮሚሽኖችን ግልጽ ውድድር፣በግብዣ ጥሪ በሚደረግ ውድድር ወይም ቀጥታ የመምረጥ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስላት ይቻላል፤ ነገር ግን ሁሉንም የዲስትሪክቱን ህጎች፣ደምቦች እና ፖሊሲዎችን ማክበር አለበት። ለቤተ መጽሀፍቱ በሚደረግ ማንኛውም አዲስ አርት(ሥነ ጥበብ) ወይም ኤግዝቢት የማህበረሰቡ ተሳትፎ በምርጫው ሂደት

ላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው። የምርጫ እና የማጽደቅ ሂደቱ በመሰራት ላይ ላሉ ቤተ መጽሀፍት አዲስ አርት(ሥነ ጥበብ) ወይም ኤግዝቢቶች፣በፕሮጀክቱ አጠቃላይ የጊዜ ማእቀፍ ውስጥ ይካተታል።

## 6. የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራ) ስጦታዎች

a. የግምገማ ኮሚቴው የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራ) ስጦታዎችን በDCPL ቤተ መጽሀፍት የአርት(ሥነ ጥበብ) ስብስብ ውስጥ ሊካተቱ የሚገቡ መሆናቸውን ለመወሰን በዲስትሪክቱ እና በDCPL ህጎች፣ደምቦች፣እና ፖሊሲዎች መሰረት ይመረምራል።
b. ሁሉም የአርት(ሥነ ጥበብ) ስጦታዎች አግባብ ካለው የDCPL አመራር ጋር በመመካከር በስትራቴጂክ አጋርነት ዳይሬክተር፣በዲዛይን አቀናባሪ እና የልዩ ስብስቦች ስራ አስኪያጅ ተቀባይነት ሊያገኙ ይገባል።
c. DCPL ያገኛቸው የአርትዎርክ(ሥነ ጥበብ ስራ) ስራዎቹ ጊዜን መሰረት ያደረጉ ወይም ጊዜያዊ ተፈጥሮ ያላቸው እና የሚገጠሙትም ለተወሰነ ጊዜ በመሆናቸው ምክንያት በስትራቴጂክ አጋርነት ዳይሬክተር አማካኝነት በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው።
    i. ለመምረጥ ከላይ ያለውን መመዘኛ በመጠቀም፣ለተለየው አውድ/ቦታ በDCPL የአርት(ሥነ ጥበብ) ስብስብ ውስጥ ለመካተት ከፍተኛ የአርቲስቲክ ዋጋ ያለው መሆን።
    ii. ከእቃዎቹ ባህሪ አንጻር የሚቆዩ ፣ምክንያታዊ፣ አደገኛ ያልሆኑ እና ሊጠገኑ የሚችሉ።
d. የDC የህዝብ ቤተ መጽሀፍት ለቤተ መጽሀፍቱ የአርት(ሥነ ጥበብ) ስጦታዎችን ለለገሱ ሁሉም ግለሰቦች፣ቡድኖች እና/ወይም ኮርፖሬሽኖች እውቅና ይሰጣል።
e. ተቀባይነት ያገኙ አርትዎርክ(ሥነ ጥበብ) ለእይታ ማቅረብ የDCPL ፍቃደ ስልጣን ነው። ለእይታ የማቅረብ ምንም ግዴታ የለም።

## 7. የትርጉም እና የተሳትፎ መመሪያዎች

a. በDCPL የተገጠመ እያንዳንዱ የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራ) ወይም ኤግዝቢት የሰራተኛ ስልጠና እና ከአርቲስቱ ጋር የህዝብ ፕሮግራሞችን ጨምሮ በትርጉም እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ምክረሀሳቦች መታጀብ አለበት። ምክረሀሳቦቹ አግባብነት ካላቸው የDCPL አመራር እና ማንኛውም የአዘጋጅ አማካሪዎች ጋር በሚደረግ ምክክር የስትራቴጂክ አጋርነት ዳይሬክተር እና የዲዛይን አቀናባሪ ሀላፊነት ነው። ተፈጻሚነቱ ባሉት ግብዓቶች ላይ የሚወሰን ነው።
b. በDCPL ለእይታ የሚቀርቡ ሁሉም ቋሚ የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራ) በተቻለ መጠን የአርትዎርኩን(ሥነ ጥበብ ስራውን) የጀርባ ታሪክ፣የማህበረሰቡ ምልከታ፣እና የአርትዎርኩ(ሥነ ጥበብ ስራው) በቤተ መጽሀፍቱ ውስጥ የተገጠመበት ምክንያትን በያዘ የማብራሪያ ጽሁፍ መታጀብ አለበት።
c. ሌላ ጠቃሚ የማብራሪያ ዓይነት፣የህዝብ ዝግጅቶችን እና በቤተ መጽሀፍቱ ሠራተኛ የሚመራ መደበኛ እና ኢመደበኛ ጉብኝቶችን ጨምሮ በፕሮግራም የሚደረግ ነው።

## 8. መድን፣ዋስትና እና ሀላፊነት

አርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዝቢቶች በእያንዳንዱ ቤተ መጽሀፍት መደበኛ አሰራር መሰረት ተገቢ የሆነ እንክብካቤ እና ጥበቃ ይሰጣቸዋል። የDCPL ሰራተኛ ኤግዝቢቶችን አይቆጣጠርም ወይም አያስቀምጥም። ኤግዝቢት አቅራቢው ለእይታ የሚቀርበው ስራ፣በሚገጠምበት፣ሲሰበር፣ወይም ከቤተ መጽሀፍቱ ወይም ወደ ቤተ መጽሀፍቱ በሚጓጓዝበት ጊዜ ለሚደረሰው ጥፋት ወይም ጉዳት ከማንኛውም ሀላፊነት ነጻ ሊያደርገው ይገባል። የDCPL ንብረት የሆኑ የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራ) በD.C. መንግስት የአደጋ አስተዳደር ቢሮ አማካኝነት ዋስትና ተገብቶላቸዋል። መድን የተገባላቸው የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራ) ዝርዝር በዲዛይን አቀናባሪው በየዓመቱ ይሻሻላል።

## 9. የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራዎች)ን ማግኘት

DCPL ያገኛቸው ሁሉም ስራዎች በDCPL የልዩ ስብስቦች ዝርዝር ውስጥ መመዝገብ አለባቸው። ስምምነቶች በDCPL ልዩ ስብስቦች ይጠበቃሉ።

## 10. የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራዎች)ን ማስወገድ

DCPL የተገኙ ሁሉንም የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራ) ለመጠበቅ ይሰራል፣ነገር ግን የDCPL ጥቅም ለማስጠበቅ ተመራጭ ሆኖ ከተገኘ ማንኛውንም እቃዎች የማስወገድ መብት ይኖረዋል። ማስወገድ አግባብነት ካላቸው የDCPL አመራር ጋር በሚደረግ ምክክር ፣የስትራቴጂክ አጋርነት ዳይሬክተር እና የዲዛይን አቀናባሪ ሀላፊነት ነው።

## 11. ጥገና እና ማስወገድ

DCPL ያገኛቸው ሁሉም የአርትዎርክ(ሥነ ጥበብ ስራዎች) የወደፊት የረጅም ጊዜ የጥገና እና የአጠባበቅ እቅድ ሊኖራቸው ይገባል። DCPL የአርት(ሥነ ጥበብ) እና ኤግዝቢት ፕሮግራም ራእይን ለማሳካት እና/ወይም በዚያ ሁኔታ ምክንያት በማንኛውም ጊዜ የአርትዎርክ(ሥነ ጥበብ) የማስወገድ መብቱ የተጠበቀ ነው። DCPL ተጽእኖ ሊኖራቸው በሚችል በእያንዳንዱ ሁኔታ ላይ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

## 12. የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራዎችን) የማስወገድ ጥያቄ

DCPL በቤተ መጽሀፍቱ ለእይታ የሚቀርቡ የአርትዎርክ(የሥነ ጥበብ ስራዎችን) በሚመለከት የዜጎችን አስተያየት ይቀበላል። እቃዎችን የማስወገድ ጥያቄ ላይ ፣በDCPL ስብስብ ላይ እንዳለው ማንኛውም እቃ በዚህ ሰነድ ላይ በተቀመጠው የፖሊሲ ዓላማ መሰረት ቤተ መጽሀፍቱ ይወስናል። አንድን እቃ ለመቃወም፣በድህረ ገጹ ላይ ያለውን[እኛን ማግኘት] የሚለውን ቅጽ ይጠቀሙ።